# ሽንፈት የወለደው የፈጠራ መግለጫ

**ፕሬስ ሪሊዝ**
**ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ/ም**
**ማስታወቂያ ሚኒስቴር**

የያዘው ዓላማ ከሽብርተኛነቱ በስተቀር የነፃ አውጭነት የማስመሰያ ካባ እንኳ ሊያላብሰው ያልቻለው ራሱን የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ወይም ኦብነግ ብሎ የሚጠራው ቡድን ጥቅምት 10 ቀን 2000 ዓ/ም ባሰራጨው ሃሰተኛ መግለጫ ከኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ጋር ዋርዴር ላይ ባካሄደው ውጊያ 140 ወታደሮችን እንደገደለ ገልጿል ፡፡ በመሠረቱ ቡድኑ በጠቀሰው ስፍራና ወቅት ከኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ጋር ምንም ዓይነት ውጊያ አላደረገም ፡፡ ይህ በስያሜው ብቻ የነፃ አውጭነት ታፔላ ለጥፎ በተግባር ግን በለየለት የሽብርተኛና ፀረ ሰላም እንቅስቃሴው የሚታወቀው ቡድን ሲያራምደው የቆየውን እኩይ ተግባር ከምንጩ ለማድረቅ የኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያ ሰራዊት በቡድኑ ላይ ፈጣንና ተገቢ እርምጃ መውሰዱ ይታወቃል ፡፡ ቡድኑ በደረሰበት ከፍተኛ ሽንፈት ምክንያት በተደራጀ መልኩ ከመከላከያ ሰራዊታችን ጋር የፊት ለፊት ውጊያ የማድረግ አቅሙም ሆነ ድፍረቱ የለውም ፡፡ የያዘው ዓላማም ሆነ አደረጃጀቱ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው አይደለም ፡፡

ቡድኑ ባልተቀናጀና በደመነፍስ በሚመራ የሽብር እንቅስቃሴው የሱማሌ ክልል ሕዝብን ሰላማዊ ኑሮ ማወክና የልማት ተቋማትን

ማውደም ዋነኛ አላማው ነው ፡፡ ለዚህም ከዚህ ቀደም በሱማሌ ክልል አንዳንድ ስፍራዎችና ከተሞች ከሻዕቢያና ኦነግ ጋር በማበር የፈፀማቸውና ኃላፊነቱን በይፋ የወሰደባቸው ፀረ ሕዝብና ፀረ ልማት የሽብርተኝነት ተግባሮቹ ምስክሮች ናቸው ፡፡ የክልሉን ሰላምና የሕዝቡን ደህንነት በአስተማማኝ ለማስጠበቅ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ክልሉን ከሽብርተኛው ቡድን ለማጽዳት ቀደም ሲል በወሰደው አርምጃ በርካታ ጀሌዎቹ መደምሰሳቸውና አንዳንድ የአመራር አባላቱን ጨምሮ ሌሎች በርካቶች ደግሞ መማረካቸው ይታወሳል፡፡ ቀሪ ኃይሉም በየፊናው ተበታትኖ ከፊተኛ ኪሳራ ደርሶበታል፡፡

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ የሽብርተኛው ቡድን ከመከላከያ ሠራዊታችን ጋር ባላደረገው ውጊያና ስፍራ " ድል " እንዳገኘ አድርጎ ያናፈሰው ሃሰተኛ ዘገባ በእጅጉ አስገራሚ ነው ፡፡ ቀደም ሲል በቀቢፀ ተስፋ ሲፈጽም በነበረው እኩይ ተግባሩ ስሙ በሚዲያ መነሳቱን እንደጀብዱና ሽልማት ቆጥሮ " አለሁ " ለማለት የተጠቀመበት ስልት በጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን ፣ በክልሉ መንግሥትና ሰላም ወዳድ ሕዝብ የጋራ ርብርብ በደረሰበት ሽንፈት ምክንያት እንደከሸበፈበት ይታወቃል ፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ጀሌዎቹ ባልዋሉበት የፈጠራ አውደ ውጊያ ድል እንደተቀዳጀ በማስመሰል ሃስተኛና የቅዠት መግለጫ ለማውጣት የተገደደው ፡

ይልቁንም አሁን በክልሉ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ አካባቢውን ከሽብርተኛው ቡድን በማጽዳት የክልሉን ሰላም የማረጋገጥና የተጀመረውን የልማት እንቅስቃሴ አጠናክሮ የማስቀጠል ተግባር ነው

፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ በሽብርተኛው ቡድን ፀረ ሰላም እንቅስቃሴ ምክንያት የተስተጓጎለውንና ለአካባቢው ሰላማዊ ሕዝብ የምግብ፣ የመድሃኒትና ሌሎች አስፈላጊ የሰብአዊ ዕርዳታዎች አቅርቦት ለማድረግ መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት ጋር ተቀራርቦ እየሠራ ነው ፡፡

ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ሽብርተኛው ቡድን በዚህ ወቅት ይህን መሰል ሃሰተኛና የፈጠራ ዘገባ ያሰራጨው መንግሥትና የሰብአዊ ድርጅቶች ለክልሉ ሰላማዊ ሕዝብ የዕርዳታ አቅርቦት ለማድረስ እየሰሩ ባሉበት ወቅት መሰረተቢስ ስጋት በመፍጠር ፕሮግራሙን ለማስተጓጎል በማለም እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ፡፡ ይህም በግልጽ የሚያረጋግጠው ቡድኑ ምን ያህል ኃላፊነት የጎደለውና በተለይም ለክልሉ ሕዝብ ደንታ ቢስ እንደሆነ ነው ፡፡ ይህ የኦብነግ የፈጠራ ዘገባም ፀረ ሕዝብነቱን በራሱ እንደበት ያረጋገጠበት ከመሆኑና አሁንም በተበተነ መንገድም ላይ ሆኖ ከሽብርተኛነት አባዜው እንዳልተላቀቀ በግልጽ ከማመልከቱ ውጭ ያስገኝልኛል ብሎ ያሰበውን ከንቱ ፖለቲካዊ ትርፍ በምንም ዓይነት መልኩ እንደማያስገኝለት በግልጽ ሊረዳው ይገባል ፡፡

በሌላም በኩል መንግሥት የክልሉን ሰላም በአስተማማኝ ለማረጋገጥና የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሴãCN ከክልሉ መንግሥትና ሰላም ወዳድ ሕዝብ ጋር በመሆን ውጤታማ ለማድረግ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል ፡፡

ꝏꝏꝏ ꝏꝏ